Tribunals Service

Asylum Support Tribunal

ራሱ የቻለ (ከሌላ ክፍል ግንኙነት የሌለው) ክፍል። ጥገኝነትን ለጠየቁ ጠይቀው እርዳታ ላልተቀበሏቸው እና የምግብና የቤት ክራይ አገልግሎት ለቆመባቸው።

# እንኳን በደኅና መጣችሁ ወደ AST (ጥገኝነትን ለጠየቁ የእርዳታ ፍርድ ቤት) ዌብሳይት

ወደ ጥገኝነት የጠየቁ የእርዳታ ፍርድ ቤት ዌብሳይቱ በመምጣታቹሁ በጣም ደስ ብሎኛል፡ የዚሁ ይዞታ ጠቃሚ እና እናንተን የሚረዳ ሆኖ እንደምታገኙት እተማመናለሁ።

የስደተኞች እና ጥገኝነት ለጠየቁ የታወጀ ሕግ 1999 አዲስ የእርዳታ አሰጣጥ ለነሱ እና በነሱ ትከሻ ላይ ለሚኖሩ የሚሆን አቋቋመ።

The Asylum Resource Directorate (ARD)(ጥገኝነት ለጠየቁ የእርዳታ ምንጭ ዋና ክፍል), አመልካች እና በነሱ ትከሻ ላይ ለሚኖሩ በችግር ላይ አሉ የሚለው ሕግ የወጣው ሁኔታቸው የሚያሟላ መሆኑን ምርመራ ያደርግ እና። ምን ዓይነት ደረጃ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው የሚወስን ነው። ARD እርዳታ ኣይሰጣችሁም ብሎ ከወሰነ፡ ወይም ደግሞ በመጀመሪያ የሚሰጣቸው የነበርው እርዳታ ካቆመ። ARD ለማቆም ከወሰነ ወይም ደግሞ ይሰጠው የነበረው እርዳታ ካቆመ። ጥገኝነት ጠያቂዎች ለዚህኛው ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

The Asylum Support Tribunal (ጥገኝነትን ለጠየቁ የእርዳታ ፍርድ ቤት) የጥገኞች ድጋፍ ፍርድ ቤት ከጊዜ የመጣውን ኣቤቱታ ግምት ውስጥ እናስገባለን፣

ከዚህ ቀጥለው ያሉት ዋና ጽሑፎች (ማስረጃዎች) ብዛት ለሚጠቀሙት ቋንቋዎች ተተርጉሞዋል። ይሄንን ደግሞ ስለ AST ዋናው ስራው ምን መሆኑን እና ይግባኝ ባላችሁበት ቀን ምን እንደሚደረግ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች እንደሚያቀርብላቹሁ ተስፋ እናደርጋለን። ከዚህ በተጨማሪ ማስረጃዎች ካስፈለጋቹሁ ያለጥርጥር ከኛ ጋር ተገናኙ።

**ሰብሃ ሃሩን ስቶሪ። (Sehba Haroon Storey)**
**የጥገኝነት እርዳታ ሐላፊ ዳኛ (Chief Asylum Support Adjudicator)(CASA)**

# መግቢያ

## የኛ ስራ ምን እንደሆነ

የኢሚግረሽንና የጥገኞች የ1999 ኣዋጅ። ጥገኞችና  በእነሱ ትከሻ ላይ ለሚኖሩ የሚሆን ኣዲስ የእርዳታ ኣሰጣጥ ኣቋቁሞዋል፣ የሄኛው ሕግ የድሮ የነበረው ጥገኝነት ለጠየቁ የሚገባቸው እርዳታ ከየጥሮታ አበል የሚሰጣቸው የነበረው እርዳታ እና ሌሎች እርዳታዎች የተቀየረ ነው።

The Asylum Resource Directorate (ARD) (ለጥገኝነት የጠየቁ የእርዳታ ፍርድ ቤት), የአመልካቹ እና በእነሱ ትከሻ ላይ ለሚኖሩ የችግራቸው መጠን ፈተና በሕጉ መሰረት የሚገባቸው መሆኑን እና ምን ያህል እርዳታ እስከ ምን ደረጃ ላይ እንደሚያስፈልጋቸው የሚወስን ነው። ይሄኛው እርዳታ የመኖሪያ ቤት እና አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች መግዣ የሚሆን ገንዘብ ሊሆን ይችላል።

ግን ARD እርዳታ መሰጠት የለበትም ብሎ ከወሰነ ወይም።  አስቀድመው ግን እርዳታውን እየሰጥዋቸው ከነበሩ።  ARD የሚሰጠው የነበርው እርዳታ ለማቆም ከወሰነ።  ጥገኝነት የጠየቅው ለዚህኛው ውሳኔ ይግባኝ ማለት ይችላል።

የ AST ይግባኝ የተባለው ጉዳይ እንዲታይ ይቀበላል። ስለ ጥገኝነት ጉዳይ ወይንም ስለ ጥገኝነት እና ስለ ስደተኞች የሚመለከት ጉዳይ ግን ለነሱ ኣይመለከታቸውም እና ስለዚህ ጉዳይ ኢያዩም።  ስለ በ ARD እርዳታ ለቆመባቸው ወይም ደግሞ እርዳታ ለማግኘት ስለሚመለከት ይግባኝ የተባለ ጉዳይ ብቻ ነው የሚያዩት።

የፍርድ ቤቱ ወሳኝ ይግባኝ ለተባለው ጉዳይ ሲያይ ከሶስቱ አንድ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል። ጉዳዩ በ Secretary of State (የአገሩ ዋና ጸሓፊ) እንዲታይ ሊወስን ይችላሉ። ወይም ደግሞ ይግባኝ ለተባለው ተቀብለው እርዳታው እዲጀምርላቸው ሊወስን ይችላል። ወይም ደግሞ ይግባኝ ለተባለው ላይቀበሉት እና ሊዘርዙት ይችላሉ።

ፍርዱ ቤቱ ውስጥ የተሰጠው ውሳኔ ለምን ምክንያት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሙሉ መግለጫ በጽሑፍ መስጠት አለበት እና ውሳኔው ደግሞ የመጨረሻ ነው።

# ይግባኝ ሲባል

ይግባኝ ሲባል (በ የ 103 ክፍል ሕግ) መሰረት ሆኖ "notice of appeal" (የይግባኝ ማስታወቂያ) የሚባል ፎርም በሙሉ በኢንግሊዘኛ ተሞልቶ መቅረብ አለበት። ፎርሙ ይግባኝ በሚለው ሰው ወይም ደግሞ (በወኪል) ተፈርሞ ውሳኔው ከተሰጠው ደብዳቤው ከ ARD ከደረሰበት ቀን ጀምሮ 3 የስራ ቀኖች (ከሰኞ እስከ ዓርብ ጊዜ) ወደ ፈራጁ ውስጥ መድረስ አለበት።

ፈራጁ የይግባኙ ጉዳይ በቃል ወይም በጽሑፍ በቀረበው ማስረጃ ሊመለከት ይችላል ይሄ ደግሞ ('"የወረቀት ጉዳይ" ፐፐር ከይስ) "papers case" ይባላል ።

ምናልባት ይግባኝ የማለት ቀን ዳኛው ሊያስረዝመው ይችላል። ትክክለኛ ፍርድ ለማግኘት ይረዳል ብሎ ካሰበ። ወይም ደግሞ ቀኑን አሳልፎ ይግባኝ የማለቱ ምክንያት ይግባኝ ለሚለው ሰው ከአቅሙ ወጪ የሆነ ሁኔታ አጋጥሞት ነው ብሎ ዳኛው ካመነበት ብቻ ነው።

የፍርድ ቤቱ ጸሐፊ ይግባኝ የሚል ደብዳቤ በደረሰበት ቀን። የ AST ወደ የአገሩ ዋና ጸሐፊ በፋክስ ዋና ወረቀቱን እና ሌላ ተጨማሪ ለጉዳዩ ሊረዱ የሚችሉ ዶኩመቶች ባንድ ላይ ይልካል።

የአገሩ ዋና ጸሐፊ በፋክስ ውይም ደግሞ በእጅ ወደ የፍርድ ቤት ጸሐፊ "appeal bundle" (የይግባኝ የተባለው ጥቅል) መላክ አለበት። የአገሩ ዋና ጸሐፊ የዚህኛው ግልባጭ በአስቸኳይ በደብዳቤ ወይም ደግሞ በፋክስ አድርጎ ይግባኝ ወደሚለው አካል ይልካል።

የይግባኝ የተባለው ጥቅል በውስጡ ይግባኝ ለማለት የተሞላው ፎርም። ሌላ ተጨማሪ የተሰጡት ማስረጃዎች እና የARD የወሰነው ውሳኔ የሚገልጥ ደብዳቤ እና ሌላ ተጨማሪ ወረቀቶች ከየአገሩ ዋና ጸሐፊ ጋር የተላኩ ለዚህኛው ውሳኔ ለመድረስ ያበቃቸው መግለጫዎች ያጠቃልላል።

ከየአገሩ ዋና ጸሐፊ የይግባኝ የተባለው ጥቅል ከተላከበት 1 ቀን በኋላ ይሄንን ቀን "consideration day" (ጉዳዩ የሚታይበት ቀን ተብሎ) ይጠራል። በዚህኛው ቀን ፈራጁ ይግባኝ የተባለው ውሳኔ የሚሰጥበት ቀን ማሳወቅ አለበት።

ጉዳዩ በቃል የሚሰማ ከሆነ። AST ለአገሩ ዋና ጸሐፊ እና ይግባኝ ላለው ሰው ይሄንን የሚካሄድበትን ቀን የተኛው መሆኑን ያሳውቃል። ይግባኝ ያለው ሰው ይግባኝ ሲል ጉዳዩ በቃል ይሰማልኝ ብሎ ፎርሙን ከሞላ እና። ወይም ደግሞ ፈራጁ ይሄንን አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነበት። ጉዳዩ በቃል እዲሰማ ያፈቀዳል። ሌሎች ይግባኝ የተባሉ በሙሉ ጉዳዮች ግን ያለ የቃል ጥያቄ ይታያሉ።

ጉዳዩ በቃል የሚታይ ከሆን ጉዳዩ ከሚታይበት ቀን ጀምሮ ውሳኔ እስከሚወሰንበት ቀን 5 የስራ ቀኖች ውስጥ መብለጥ የለበትም። ሌሎች ጉዳዮች ግን በብዛት በጉዳዩ የሚታይበት ቀን ውሳኔ ይሰጣል ወይም ደግሞ በተቻለ መጠን በተሎ (ግን ውሳኔው ለመስጠት ጉዳዩ ከታየበት ቀን ከአምስት የስራ ቀኖች ማለፍ የለበትም)።

# ይግባኝ የተባለው ውሳኔ ሲወሰን

ዳኛው ጉዳዩን ይመለከታል የሚላቸውን ነገሮች በግምት ውስጥ ያስገባል። (በተጨማሪም ሁኔታዎች ይግባኝ ከተባለ በኋላ ይግባኝ ላለው ሰው የደረሱት ነገሮች)።

ጉዳዩ በቃል የሚሰማ ከሆነ ዳኛው የቀኑን ውጤት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሰዎች ሁሉ ከነዳኞቻቸው ጋር እዛው ውጤቱ ማሳወቅ አለበት።

ጉዳይ በሚታይበት ቀን ይግባኝ ያለው ሰው ወይም ደግሞ ወኪሉ (ወኪል ካለው) ወይም ደግሞ የአገር ዋና ጸሐፊ በዚህ ቀን ውስጥ ባይገኙም ያለነሱም ጉዳዩ ይሰማል። የጉዳዩ ውሳኔ በሚሰጥበት ቀን ይግባኝ ያለው ሰው ወይም ወኪሉ (ወኪል ካለው) እና የአገር ዋና ጸሐፊ ፍርድ ቤት ውስጥ ባይገኙም ውሳኔው ጉድዩ ከታየ በኋላ ይላከላችዋል።

ይግባኝ ከተባለበት ጉዳይ የውሳኔ ቀን በኋላ 3 ቀናት ውስጥ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ወዳለው ሰውና እና ወደ Secretary of State's (የአገር ዋና ጸሐፊ) የውሳኔው ውጤትና ለምን ለዚሁ ውሳኔ መድረስ እንደቻሉ መግለጫ ይልካል። “የውሳኔ መግለጫ” ማለት በጽሑፍ ሆኖ ለምን እዚሁ ውሳኔ እንደደረሱ የሚገልጥ ነው። ወሳኔው ይግባኝ ለአለው ሰው የማይስማማ ከሆነ ማለት ውጤቱ የጠበቁትን ውጤት ካልሆነ ይግባኝ ያለው ሰው ሌላ የሚወስደው እርምጃ ካለ AST ውጤቱን እና መግለጫውን ይግባኝ ለአለው ሰው በሚገባው ቋንቋ አስተርጉሞ ወረቀቱን ወጤቱ ከተሰጠበት ቀን ብዙ ግዜ ሳይወስድ ያዘጋጃል።

እባካችሁ አስታውሱ ይግባኝ ያለው ሰው በድንብ እንግሊዘኛ ከሚያወራ ሰው ጋር የሚኖር ከሆነ ወይም ደግሞ ጥሩ ወኪል ካላቸው እንደ ጠበቃ ወይም ደግሞ ለስደተኞች የሚረዳ ድርጅት ሌላ የመንግስት ድርጅት ያልሆነ ካላቸው። ይግባኝ የተባለው ውጤቱ እና የውጤቱ በግለጫ ወደ ሌላ ቋንቋ አይተረጎምም።

# ይግባኝ ማለት ካልተቀበሉት

የአገር ዋና ጸሐፊ)ይግባኝ የተባለው አልቀበልም ብሎ ውሳኔው ካወጣ ለዳኛው እና ይግባኝ ላለው ሰው ባስቸኳይ ማሳወቅ አለበት።

ይግባኝ ያለው ሰው ጉዳዩ አልጨርሰውም እተወዋለሁ የሚል ከሆነ ባስቸኳይ ለፍርድ ቤቱ እና ለ የአገር ዋና ጸሐፊ ውሳኔው ማሳወቅ አለበት።

ከባለጉዳዮቹ አንዱ ጉዳዩ ማቆም በሚወስኑበት ግዜ ወይ በተሰጣቸው ውሳኔ ምክንያት ወይም ደግሞ ጉዳዩ ስለተዘጋ። ጉዳዩ እንደተጨረሰ ተደርጎ ይታያል።

# ተጨማሪ መረጃ

ይግባኝ ያለው ሰው ተጨማሪ ማስረጃዎች ካላቸው እና ይሄንን ማስረጃ ዳኛው እንዲያይላቸው ከፈለጉ። የዚሁ ማስረጃ ግልባጭ ለAST ና ARD ባስቸኳይ መሰጠት አለበት። የሚያቀርቡት ማስረጃዎች ከእንግሊዘኛ ቋንቋ የተለየ ከሆነ ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉሞ ተረጋግጦ መቅረብ አለበት።

ይግባኝ ያለው ሰው ተጨማሪ ማስረጃዎች ማቅረብ የሚችለው እንደ ደብዳቤ። ሰነድ እና የጤና ሪፓርት ወይም ደግሞ ደረሰኝ እና ፋክቱር ጉዳዩን ይረዳል ተብሎ የሚገመቱ ከሆነ ነው። ጉዳዩን ይመለከታል ብለው የሚያስቡት ነገሮች ሁሉ መላክ ይችላሉ። ጉዳዩን ይረዳል ይሆናል ብለው የሚጠራጠሩ ከሆነም ዝም ብለው ይላኩት እና ዳኛው ማስረጃው አይቶ ይወስናል። ግልባጩ አስቀድሞው ልከውት ቢሆንም ይግባኝ ያለው ሰው ጉዳዩ በሚታይበት ቀን ዋናው (ኦሪጂናል ዶኩመንት) ማስረጃው ይዘው መምጣት አለባቸው።

# ይግባኝ ያሉት ጉዳይ በትክክል እንዲካሄድ

ይግባኝ ያለው ሰው ወይም ደግሞ ወኪሉ ጉዳዩ በሚሰማበት ቦታ መምጣት ከፈለጉ በግዜ (በሰዓቱ) መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው። አንደኛቸው ቢቆይም ዳኛው ጉዳዩ ለነሱ ሳይጠብቅ ሊቀጥል ይችላል። የዳኛው ውሳኔ የመጨረሻ ነው። እና መልሶ ይግባኝ የማለት እድል የለም ሰለዚህ ጉዳዩ በሚሰማበት ቀን በሰዓቱ መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው።

ይግባኝ ያለው ሰው አድራሻው ወይም ደግሞ ወኪላቸው ከቀየሩ ለጥገኝነት ለጠየቁ የእርዳታ ፍርድ ቤት ARD ባስቸኳይ ማሳወቅ አለባቸው። ይሄንን AST በደብዳቤ በፋክስ ወይም ደግሞ በቴሌፎን ስልክ በመደወል ልታገኝዋቸው ትችላላቹሁ።

ወደ AST ደብዳቤ ስትጽፉ እባካቹ የይግባኝ የተባለው የመዝገብ ቁጥር እና ጉዳዩን የሚሰማበት ቀን በሁሉም ደብዳቤዎቻችሁ አስፍሩት።

# በየዓይነቱ

### ተቀባይነት የሌለው ይግባኝ

እባክዎትን ያስተውሉ የውሳኔውን ቀን ያልተጻፈበት እና የ ARD የውሳኔ ደብዳቤ ቅጂ ያላያያዘ የይግባኝ ደብዳቤ ተቀባይነት እንደሌለው ባፈጣኝ ይወሰናል ስህተቱ እስከሚታረም ድረስ። እርማት ለማድረግ 7 ቀናትን እንሰጣለን።

### መመሪያ

ዳኛው ለፍርድ ይጠቅማል ወይም ይረዳል ብሎ ካመነበት ከይግባኙ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ለሚነሱት ጉዳዮች ለማንኛውም መመሪያ ሊሰጥ ይችላል።

# የይግባኝ ሂደት - የመጀመሪያው እርምጃ

ለ AST ይግባኝ በምትሉበት ጊዜ መጀመሪያ የምናረጋግጠው የይግባኝ ማድረጊያው ፎርም በትክክል መሞላቱን ነው። ፎርሙ በእንግሊዝኛ መሞላት አለበት። በእርስዎ ተፈርሞ ብተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ አለበት። ፎርሙ በትክክል ካልተሞላ ተቀባይነት አይኖረውም። ይህ ማለት ደግሞ ይግባኝ ያላችሁት ጉዳይ ፎርሙን በደምብ እስኪሞላ ድረስ አይታይም ማለት ነው (በተሰጠው የግዜ ገደብ ውስጥ)።

ፎርሙ ከታየ በኋላ ለይግባኛችሁ ፋይል ይከፍትላችኋል በኮምፒዩተራችንም እናስፍረዋለን። ይግባያችሁ የራሱ የሆነ ቁጥር ይኖረዋል። (ሁሉም የይግባይ ቁጥራችን በ "AST" ቅጥል ይጀምራል። አግኝታችሁ በምታነጋግሩን ጊዜ ይሄን ቁጥር መጥቀስ ኣስፈላጊ ነው።)

እኛም ARD ን ይግባኝ ማለታችሁንና ጉዳያችሁን ላለመቀበል ወይም ለመዝጋት የተጠቀሙበትን ዶክመንቶች ሁሉ ቅጂ እንዲልኩልን እንነግራቸዋለን።

ዳኛው ጉዳያቹሁን ኣይቶ ለተጭማሪ ማስረጃ እርስዎን ወይም ARD ን ጥያቄ መጠየቅ ይችላል። ተወካይ ካለዎት። የጥያቄዎቹ ቅጂ ይላክለታል።

ጉዳያችሁ በቃል እንዲታይላችሁ ከጠየቃችሁ። የሚታይበትን ማስታወቅያ እንልክላቹሃለን። ይህ ጉዳያችሁ የሚታይበት ቀን ሰዓትና ቦታ ይነግራቹሃል። ተወካይ ካላችሁ ለሱም የማስታወቅያው ቅጂ ይላክለታል።

ኣስተርጓሚ የሚያስፈልጋችሁ ከሆነና የምን ቋንቋ እንደምትፈልጉ እባክዎት በይግባኝ ፎርሙ ላይ ይንገሩን (ከተቻለ)። ከማንም ጋር ግንኙነት የሌለው አስተርጓሚ ጉዳዩ ለሚታይበት ቀን እናቀርብልዎታለን።

ስለ AST እና ጉዳዩ ሰለሚታይበት ማዕከል የሚያስረዳ ጽሑፍ እንልክልዎታለን። ይሄን እንዴት ልታገኙን እንደምትችሉ። የምንጠቀምባችውን ነገሮች እና አንዳንድ ቃላቶችን ይገልጽላቹሃል። የምትሉትን ለመስማት የሚያስችለን ጽሑፍም እንልክላቹሃለን።

አቅም ማነስ (አካለ ስንኩልነት) ወይም ልዩ ፍላጎት ካልዎት ለትብብር እንዲመችን አስቀድመው ይንገሩን።

# ጉዳያችሁ በሚሰማበት ቀን

ጉዳዩ እሚታይበት ቦታ ሲደርሱ ልክ እንደ ኤርፖርት እና ሌሎች ትልልቅ ህንጻዎች በፍተሻ መሳሪያዎች እንዲያልፉ ይጠየቃሉ። ረሰፕሽኑ ጋር ያሉት ሰራተኞች እንደ ሞባይል እና ሲጋራ እና ላይተር ሌሎች ዕቃዎች እዛው ከነሱ ጋር ትተዎት እንዲገቡና ጉዳያቹ ጨርሳቹ ስትወጡ ይመልሱላችኋል።

ጉዳያቹ ሊሰማ ሲቀርብ አስተናባሪው ወደ አንደኛው ደረጃ የሚገኘው ጉዳያቹ የሚሰማበት ቦታ እናንተ እና (ወኪል ካላቹም) እንድትሄዱ ይጠይቃችኋል። እርስዎ አስተርጓሚው እና ወኪሉ ከ ARD በክፍሉ አጠገብ (ኮሪዶሩ) ጋር እንድትጠብቁ ዳኛው እስከሚዘጋጅ ድረስ አስተባባሪው ይተይቃችኋል።

ዘመድ ውይም ደግሞ ጓደኛ ይዘው ከመጡ በክፍሉ ውስጥ መግባት ይችላሉ ግን ወደ ኋላ ቁጭ ብሎ መጠበቅ ነው እንጂ ጉዳዩ ውስጥ መግባት አይፈቀድላቸውም። ምስክር የሚሰጥ ሰው ይዘው መጥተው ከሆነ ደግሞ፡ እዛ ማረፊያ ክፍል ሆኖው እስከሚጠሩ ድረስ እንዲጠብቁ ይጠየቃሉ።.ምስክር የሚሰጡበት ሰዓት ከደረሰ አስተናባሪው ይዘዋቸው ይገባል። አስፈላጊው ዝግጅት እንድናደርግ እባካቹ ምስክር የሚሰጥ ይዛቹ የምትመጡ ከሆነ አስቀድማቹ አሳውቁን።

ጉዳዩ እየተሰማ እያለ ጉዳዩ የሚያቀርብ ጸሐፊ የ ARD የበፊቱ ውሳኔ ምን መሆኑን ይገልጣል። ጥያቄ ስትጠየቁ ሃሳባቹ እንድትገልጡ እድል ይሰጣችኋል ። አስተርጓሚ እንዲደረግላቹ ጠይቃቹ ከሆነ በስተርጓሚው አድርገው ጥያቄዎች ይጠይቁዋችኋል። ዳኛው በተቻለው መጠን በጉዳያቹ ውስጥ እንድትካፈሉ እና ሁኔታው እየተከታተላቹ መሆናቸው ያረጋግጣል።

ጉዳዩ ተሰምቶ ካለቀ በኋላ ዳኛው ስለ ይግባኝ የተባለው ውሳኔ ለመስጠት ሓሳቡ እስከሚጨርስ ድረስ ወደ ማረፊያ ክፍል እንድትጠብቁ ትጠየቃላቹ።

ልክ ዳኛው ወሳኔ ለመስጠት ከተዘጋጀ በኋላ ጉዳያቹ ወደ ተሰማበት ክፍል እንድትመለሱ ትጠየቃላቹ እና ዳኛው ውሳኔው ምን መሆኑን ያስረዳችኋል ዳኛው ውሳኔው ይግባኝ የተባለውን ሊቀበለው ይችላል። ወይም ደግሞ ጉዳዩ ወደ (የአገር ዋና ጸሐፊ) እንዲመለስ ሊወስን ይችላል ወይም ደግሞ ይግባኝ ማለቱ ላይቀበለው እና ጉዳዩ ሊዘጋው ይችላል።

ጉዳዩ የታየበት ክፍል ለቃቹ ከመውጣታቹ በፊት የተነገራቸው ውሳኔ በጽሑፍ ይሰጣቸዋል። በሁለት ቀን ውስጥ ደግሞ የውሳኔወ መግለጫ (መግለጫ ጽሑፍ) በደብዳቤ ይላካላችኋል። አስፈላጊ ከሆነ መግለጫው በሚገባቹ ቋንቋ እናስተረጉሙላችዋለን። ጉዳያቹ የተሰማበት ከትንሽ ቀኖች በኋላ መግለጫው ይላካላችዋል። ይሄንን እንዲደርሳቹ እባካቹ አድራሻቹ ቀይራቹ ከሆነ አሳውቁን። ጉዳያቹ በሚታይበት ቀን ደግሞ በፎርሙ የአሁኑ አድራሻቹ እንድትሞሉ ትጠየቃላቹ።

ጉዳያቹ ታይቶ ካለቀ በኋላ ከቦታው ከመውጣታቹ በፊት እባካቹ እዛ ረሰብሽን የተዋቹት እቃዎቻቹሁ ይዛቹ ለመሄድ አትርሱ።

# ፐይፐር ከይስ (የወረቀት ጉዳይ)

ጉዳያቹ በቃል እንዲሰማላቹ ያልጠየቃቹ ከሆነ፡ ይግባኝ ያላችሁት ውሳኔ መልስ ወረቀታቹ ከ ARD ከደረሰን በኋላ እስከ አምስት ቀን ሊወስድ ይችላል።. በተጨማሪም ከARD ወይም ደግሞ ከናንተ ተጨማሪ ማስረጃ ሊጠየቅ ይቻላል።. ወኪል ካላቹሁም የተጠየቃቹ ግልባጭ ይላክለታል። ጉዳያቹ ዳኛው ከወሰነው በኋላ

የመግለጫው ዝርዝር እንልክላችዋለን። አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ወደ ምትናገሩት ቋንቋ እናስተረጎምላችዋለን።

# የምንጠቀምባቸው ቃላቶች መግለጫ (መምሪያ)

አንዳንድ የምንጠቀምባቸው ቃላቶች ምናልባት ያልለመዱት ሊሆኑ ይችላሉ። በታች የሚቀጥለው ክፍል የነዚህ ቃላቶች መግለጫ ነው። ያልገባቹ ነገር ካለ እባካቹ የእርዳታ ስልክ (ሄልፕ ላይን) ቁጥር (020) 8588 2500 አድርጋቹ ስልክ ደውሉልን።

ይሂኛው ማስታወቂያ ወረቀት በተለያዩ ቋንቋዎች አዘጋጅተነዋል። የሚያስፈልጋቹ ከሆነ እባካቹ ይግባኝ የሚባልበት ክፍል ጋር ተገናኙን። ይሂንን ማስረጃ ወረቀት በቀላሉ እንግሊዘኛ ልንገልጠው ሞኩረናል። አትርሱት ያልገባቹ ነገር ካለ እኛን ጠይቁን እዛ ይግባይኝ የሚባልበት ቦታ ተገናኙን። ወይም ደግሞ ለወኪላቹ ጠይቁት።

# A

## በፍርድ ቤት ማስወሰን

ዳኛው ጉዳዩ አይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት።.

## ዳኛ

ጉዳዩ አይቶ እርዳታው መሰጠት አለበት ወይም ደግሞ የለበትም ብሎ የሚወስን።

ዳኛዎች በሙሉ ራሳቸው የቻሉ ናቸው። ይሄ ማለት ደግሞ ይሄንን ውሳኔ መሰጠት አለበት ብሎ የሚነግራቸው ሰው የለም። የሚወስኑት ውሳኔ ሕግ ተከትለው ነው።

ዳኛዎቹ በምሉ ብዙ የስራ ልምድ ያላቸው ካሁን በፊት ጠበቃዎች የነበሩ ናቸው።

## ይግባኝ

ይግባኝ ማለት ዳኛውን ጉዳይህን መልሶ እንዲያየው መጠየቅ ማለት ነው።

## ይግባኝ ያለው ሰው

ይግባኝ ያለ ሰው። ለ ARD ይግባኝ ያለው ማለት ነው።

## የAST ሰራተኞች

በ AST ስር ተቀጥረው የሚሰሩ የኛ ሰራተኞች ናቸው።

ጥገኝነት ለጠየቁ የእርዳታ ምንጭ ዋና ክፍል ጉዳዩ የሚያቀርብ ባለሥልጣን (ጸሓፊ) **Asylum Resource Directorate Presenting Officer**

ከ ARD ክፍል የመጣ ይግባኝ የተባለው ጉዳይ ለዳኛው የሚያቀርብ ባለሥልጣን (ጸሓፊ) ነው።

(ጥገኝነትን ለጠየቁ የእርዳታ ፍርድ ቤት)

በዚሁ ስም ነው የምንጠራው። አንዳንዴም AST ተብለን እንጠራለን።

# C

## የማእከሉ የሥራ አስኪያጅ

የማእከሉ የሥራ አስኪያጅ ባለሥልጣን ህጋዊ ነው። ዋና ሓላፊነቱ ማእከሉ በትክክል እና በደንብ እንዲሰራ ማረጋገጥ ነው። የማእከሉ የሥራ አስኪያጅ እኛ ጋር ለሚሰሩት ሰራተኞች ሓላፊ ነው። የማእከሉ የሥራ አስኪያጅ ሰራተኞች ለዳኛው የሚያስፈልገውን ወረቀቶች ለማዘጋጀት ይረዳሉ። ግን ይግባኝ ስለተባለው ጉዳይ ውሳኔ መስጠት አይችሉም። ስራቸው ስራው በደንብ እና በትክክል እንዲሰራ የሚረዱ ናቸው። እባካቹ አስታውሱ የማእከሉ የሥራ አስኪያጅ ይግባኝ በተባለው ጉዳይ ምንም ጣልቃ መግባት አይችልም። ኣንድ የተበላሸ ነገር ቢኖር እባክዎን የማእከሉ ስራ ኣስኪያጅን ለማነጋገር ይጠይቁ፣ ።

## ሲትዘንስ አድቫይስ ቢሮ

ይሄ ሲትዘን አድባይስ ቢሮ ተብሎ የሚጠራው ድርጅት በብዛት በከተማው ውስጥ ይገኛል። ችግር ላለው ሁሉም ሰው ምክር በመስጠት የሚረዳ ነው። .ምክር ሲሰጡም ያለክፍያ ነው (ኣያስከፍሉም)። ችግራችሁ በጣም ከባድ ከሆነ ወደ ጠበቃ ወይም ደግሞ ስለችግራቹ በተመለከተ ብዙ የስራ ልምድና እውቀት ወደ አለው ጋር ያስተላልፏችኋል።

## መስቀለኛ- ጥያቄ

ጉዳዩ በሚታይበት ቀን በመጀመሪያ ይግባኝ ያለው ሰውና ምስክር ለመስጠት የመጡት ሰዎች ጥያቄዎች ይጠየቃሉ። ጥያቄዎቹን መልሳችሁ ከጨረሳቹ በኋላ ሌላው ክፍል ደግሞ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ሊጠይቅ ይችላል። መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ተብሎ የሚጠራው ይሄ ነው።

# D

## ይግባኝ ያሉትን ሲሰረዝ

ይሄንን ውሳኔ የዳኛው አንዱ ውሳኔ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ዳኛው የጥገኝነት የጠየቁ የእርዳታ ምንጭ ዋና ክፍል ARD የሰጠው ውሳኔ ተቀብሎታል ነገር ግን ይግባኝ ያለው ሰው አልተቀበለውም ማለት ነው። ዳኛው ወደዚሁ ውሳኔ የሚደርሰው ይግባኝ የተባለውን ጉዳይ በደንብ ካጠና በኋላ ነው።

# G

## ይግባኝ ያሉበት ምክንያት

እነዚህ ይግባኝ ያላችሁበትን  ምክንያቶች ናችው።

# H

## የአገር ውስጥ ዋና ጸሓፊ (Home Secretary)

የአገር ውስጥ ዋና ጸሐፊው የመንግስቱ ሚኒስትር ሆኖ የሆም ኦፊስ ሃላፊነት የሚወስድ ነው። እሱ ወይም እርሷ አንዳንዴ የሃገር ዋና ጸሓፊ (Secretary of State) ተብለው ይጠራሉ ጥገኝነት ለጠየቁት እርዳታ ጉዳዮች የአገር ውስጥ ዋና ጸሐፊው ነው።

# I

## የስደተኞች ምክር ሰጭ አገልግሎት *(Immigration Advisory Service)*

የስደተኞች ምክር ሰጭ አገልግሎት ምንም ገንዘብ የማይከፈልበት ስለ ስደተኞችን የተመለከተ ጉዳይ ለስደተኞች ምክር ይሰጣል።

## ፍርድ ቤት ውስጥ

ፍርድ ቤት ውስጥ ማለት። ሰዎች ፍርድ ቤት ውስጥ ሲገቡ እና ጉዳያቸው እየተሰማ ባለበት ግዜ ማለት ነው። የፍርድ ቤት ክፍል ማለት ጉዳዩ የሚሰማበት ክፍል ማለት ነው።

# N

## ጉዳዩ የሚታይበት ቀን ማስታወቂያ

ጉዳያቹ የሚታይበት ቀን ማስታወቅያ ማለት እኛ የምንልክላችሁ ጉዳያቹ መቸ እንደሚያይ የሚገልጽ ነው። ቀኑን እና ሰዓቱን በተጨማሪም ይግባኝ ያላችሁት ጉዳይ የት እንደሚታይ ነው። ማድረግ የሚገባችሁን ነገሮች ይገልጥላችኋል።

# P

## Papers Case (የወረቀት ጉዳይ)

ይሄንን ማለት ደግሞ ዳኛው ጉዳያቹ ይግባኝ ያላችሁት በደንብ ያነበና (ያጠና) እና እርሱ ውይም ደግሞ እስዋ እናንተ ወደ ፍርድ ቤት ሳትሄዱ ስለ ይግባኝ ያላችሁት ጉዳይ ውሳኔ ሲወስኑ ነው።

# R

## ጉዳያቹ መልሰው እንዲታይላቹ መጠየቅ

ይሄንን አንዱ ዳኛው ሊወስነው የሚችል ውሳኔ ነው። ይሄ ማለት ደግሞ ጉዳያችሁ በ ARD መልሶ እንዲታይላቹ ሲጠይቅ ነው።

## የስደተኞች የሕግ ማዕከል/የስደተኞች አማካሪ Refugee Legal Centre/Refugee Council

የስደተኞች የሕግ ማዕከል/የስደተኞች አማካሪ (Refugee Legal Centre/Refugee Council) ምክር ያለክፍያ ጥገኝነትን በተመለከተ የሚሰጥ ነው።

## ወኪል

ወኪል ለማድረግ በደንብ (በጥንቃቄ) ማሰብ አለባችሁ። ምክንያቱም ስለ ይግባኝ ያላችሁት ጉዳይ በጣም ሊረዱዋቹ ይችላሉ።

ወኪል ጠበቃ ወይም ደግሞ ፍርድ ቤት ውስጥ ከዳኛ ጋር ሊከራከርላቹ የሚችል ሰው እና ስለ ይግባኝ ያላችሁት ጉዳይ ብዙ የስራ ልምድ ያለው ሊሆን ይችላል። ምናልባት ባንድ ላይ የተሰበሰቡ ወኪል ሊሆኑ ይችላሉ። እንደ የስደተኞች የምክር አገልግሎት እና የሕግ ማዕከል/የስደተኞች አማካሪ (Legal Centre/Refugee Council) ወይም ደግሞ የሕግ ማዕከል ወይም ሲትዘን አድቫይስ ቢሮ (Law Centres or Citizen's Advice Bureau) የሚባሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

ማረጋገጥ ያለባቹ እናንተን የመረጣችሁት ሰው በደንብ አድርጎ እንዲረዳቹ የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት። ስለዚሁ ጉዳይ ለሚረዳቹ (ወኪል) ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጋችሁ ሲትዘን አድቫይስ ቢሮ ወይም ደሞ ሎው ሰንተር ( Law Centre) ጋር ስልክ መደወል ወይም መሄድ ትችላላቹ። በተጨማሪም በብዛት ቤተ መጻሕፍት የጠበቃዎች መዝገብ አላቸው።

## መልስ ሰጭ

መልስ የሚሰጠው ማለት ውሳኔው ያልተቀበለው እና ይግባኝ ሲባል ጉዳዩ በሱ ይሚያልፍ ነው። የአገር ዋና ጸሐፊው የሁልንም ይግባኝ የጥገኝነት ድጋፍ ፍርድቤት የመጣለት ይግባኝ መልስ ሰጪ ይሆናል፣

# S

## የአገር ዋና ጸሐፊ (Secretary of State)

ይሄንን የውስጥ አገር ዋና ጸሐፊ (Home Secretary) ሌላ ስም ነው። በብዛኛው የመንግስት ክፍሎች የአገር ዋና ጸሐፊ አለ። ግን AST ይግባኝ ሲል የአገር ውስጥ ዋና ጸሐፊ ብሎ ነው የሚጠቀመው ግን ሁለቱም አንድ ናቸው።

## ጠበቃ

ጠበቃ እና የሕግ ባለሞያ አንድ ነው። አንዳንዶቹ ልዩ የስራ ልምድ አላቸው። ለምሳሌ ስለ ጥገኝነት የጠየቁ ስለ እርዳታ የሚመከት።

## ማቅረብ

ማቅረብ ማለት ሁለቱ ክፍል ሰለጉዳዩ ምን እንደሚመስላቸው ባጠቃላይ ሲያቀርቡ ነው። ይሄንን የሚቀረበው ይግባኝ የተባለው ጉዳይ ታይቶ በመጨረሻ ላይ ነው። አመልካቹ እና ምስክር የሚሰጡትን ተናግረው ከጨረሱ በኋላ ነው። ይሄንን የሚደረገው ለዳኛው የሁለቱንም (ይግባኝ ያለውና ምስክር የሰጠው) ዋና ነጥቦች በደንብ አድርጎ እንዲገነዘበው ለማድረግ ነው።

# U

## ይግባኝ የተባለውን ማስከበር

ይህ ዳኛው ሊሰጣቸው ከሚችሉ ውሳኔዎች አንዱ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ዳኛው ከሚያከራክሩዋችሁ ነጥቦች ሁሉም ወይም ግማሽ ጋር ተስማምተዋልና ለጠየቃችሁት የጥገኝነት ጠያቂ እርዳታ አዲስ ውሳኔ ይሰጣል ማለት ነው። ዳኛው ውሳኔ ላይ የሚደርሰው ጉዳያችሁን ከተመለከተ በኋላ ብቻ ነው።

## አስተናባሪ

አስተናባሪ ማለት ባለስልጣን ሆኖ ዳኛውን ጉዳዩ በሚሰማበት ክፍል ውስጥ የሚራዳ ነው። እርሱ ወይም እርሷ ጉዳያችሁ ከመስማታችሁ በፊት የት መጠበቅ እንዳለባችሁ የሚነግርዋችሁ ናቸው። እርሱ ወይ እርሷ አንዳንድ ጊዜ በጓድ ጥበቃ ይረዳሉ።

# W

## ምስክር

እነዚህ ሰዎች ጉዳያችሁ በሚታይበት ቀን እናንተን ለመርዳት መጥተው ምስክር እንዲሰጡላቹህ የጠቃቹሃቸው ወይም ጉዳያችሁ በሚያቀርበው ሰው (Presenting Officer) ክርክሩን እንዲደግፉ የተጠሩ ናቸው። ምስክርን ማምጣት አያስፈልጋችሁም ነገር ግን ከፈለጋችሁ ማምጣት ትችላላችሁ። ስለዚህ ጉዳይ ወኪላችሁን ማነጋገር ትችላላችሁ። .

# ASTን መገናኘት ከፈለጋችሁ

## አድራሻ

Asylum Support Tribunal
Christopher Wren House
113 High Street Croydon
CRO 1QG

## ስልክ ቁጥር

020 8588 2500

## ፋክስ ቁጥር

020 8588 2519

## ገንዘብ የማይከፈልበት ስልክ ቁጥር

የ AST ገንዘብ የማይከፈልበት ስል ቁጥር **0800 3897913 ነው።**

ይሄንን ስልክ ቁጥር ይግባኝ ለማለት ለሚፈልጉና። ይግባኝ የማለት መንገድ ለማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች ብቻ ነው።

## ኢ- መይል

እባካችሁ አስታውሱ በአሁኑ ግዜ በኤሌትሮኒክ (ኢ.መይል) ጋር ልንገናኛችሁ አንችልም።

ከእኛ ጋር መነጋነር ከፈለጋችሁ በስልክ ወይም ደግሞ በጽሑፍ ተገናኙን።

## እንዴት አድርጋቹ ልታገኙን ትችላላቹ?

እባካቹ አስታውሱ ለጥገኝነት የጠየቁ የእርዳታ ፍርድ ቤት (Asylum Support Tribunal) ራሱ የቻለ የጠረፍ እና ከ የስደተኞች ድርጅት (Border & Immigration Agency) ምንም ግንኙነት የሌለው ነው። እባካችሁ ኣስተውሉ የጥገኝነት የጠየቁ የእርዳታ ፍርድ ቤት ከጠረፍ እና የስደተኞች ድርጅት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ወደ ክሪስቶፈር ረን ሃውስ (Christopher Wren House) ስትመጡ ወደ ዋና መንገድ በኩል መምጣት አለባችሁ እና ከዊት ጊፍት ሰንተር (Whitgift Centre) (ዋናው ትልቁ ሱቅ) ወደ ኋላ ትታችሁ መጓዝ አለባችሁ። እና AST ሕንፃ ኢስት ክሮይዶን (East Croydon) ከሚባለው የባቡር ማረፊያ የ10 - 15 የእግር ጉዞ ነው።